ግልጽ ደብዳ ቤ

ሮም፣ ነሀሴ 15 ቀን 1995 ኢ.ም.

ዶር አድማሱ ገበየሁ- አቶ ልደቱ አያሌው
አቶ ታይሉ ሻውል
ልኡል ራስ መንገሻ ስዩም
ኮል ጎሹ ወልዴ

አዲስ አበባ

1. ከሁሉ አስቀድሜ የማክበር ሰላምታዬን አቀርባለሁ። ከጥቂት ሳምንታት ወዲህ በመሀላችሁ የተፈጠረውን ትብብርና ፍጻሜ የደረሰም ሆነ በመፈጸም ላይ ያለውን ውህደት ለሀገራችን
ለኢትዮጵያ መልካም ምኞት ላለን ሁሉ የኩራት የደስታና የተስፋ ምንጭ ሆኑል።

ጥንታዊቾ ታላኀ ኢትዮጵያ ፤

2. ሀገራችን ኢትዮጵያ የሰው ልጅ የሰልጣኔ ምንጭ አንዋ በመሆኑ
የኢትዮጵያ ህዝበ መንግስት ከተፈጠረ ብዙ ሺ ኣመታት በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በእርሻ
ስልተ ምርት መኖር ከጀመሩት እጅግ ጥንታዊ ማህበረሰቦች አንዱ በመሆኑ በእርሻ ቴክኖሎጂ እድገት መሪዎች ከነበሩት አንዱ በመሆኑ በሚያፈራቸው ሰብሎች፣ ጥራጥሬና በከብት ማርባት የመጀመሪያውን ረድፍ የያዘ በመሆኑ ፤ የኢትዮጵያ ገበሬ የሰው ልጅ ምግብ ብሎ ከያዛቸው የምግብ ሰብሎች
ቅመማ ቅመማት ለማዳ እንሰሳት ያበረከትናቸው ዛሬ በሳይንሳዊ ጥናት እየተረጋገጡ ነው። ይህም በብዙ ሺህ ኣመታት የሚቆጠር የእርሻ ቴክኖሎጅ እድገት ለመሬታችን የሚስማማውን ሰብል
በመምረጥ፣ከኣመታት ወደ ኣመታት በማሻሻል፤ የሰብል በሽታዎችን የዝናብ አጦትና ድርቅ መጎትም የሚችሉትን ጥራጥሬና ሰብሎች፣ እንሰሳትን በማዳቀልም ሆነ፣ የሚመቻችውን የአየር
ጠባይና አፈር በመምረጥ ከዘመን ወደ ዘመን እያሻሸልን መጥተን እስከ ዛሬ በኣለም ላይ የሚደነቁ የምግብ ሰብሎችን ለሰው ልጅ አበርክተናል። እንዲያው በአጠቃላይ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ገበሬ በወቅቱ የኣለም ህዝብ የደረሰበትን ስልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ እንደ ነበር ሳይንሳዊ ተመራማሪዎች ያረጋግጣሉ። (መላኩ ወረደን ይመልከቱ)

3 በዚህም ረገድ ኢትዮጵያ በጎንጎና በፊደል፣ በተለይም የሴማውያን ጎንጎን በተመለከተ -ግእዝ 4000 ኣመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ቅርጹ ሰዋሰውና የቃላት ብዛቱ ከፍተኛ
እድገት የደረሰ ከመጀመሪያዎቹ ጥንታዊ የሰው ልጅ ጎንጎዎች አንዱ መሆኑ ይታወቃል። እንዲያውም አትየጵያ የሴማውያን ጎንጎ ምንጭ ናት ብለው የሚከራከሩ ከጎንጎ ተመራማሪዎች ዋና ዋናዎቹ ይገኙበታል። «<u>አልፋ ቤት</u>» የተባለው የፊደል መጠሪያ ከኢትዮጵያና ከፎኒሽያን ሴማውያን የፊደል ምልክቶች እንደተወሰዱ ይታመናል። ስለዚህም የኢትዮጵያ ባህል መሰረቱ እስስ ዘሬም ድቁረስ ከጥንት ተያይዞ የመጣው የ<u>ግእዝ ባህል</u> ነው። ስለ ግእዝ ባህል ወደ ፊት እንመለስበታለን።

4 ሮማና ፋርስ ተወዳዳሪ የኣለም ታያላን በነበሩበት በመጀመሪያው የክርስትና ዘመን ኢትዮጵያ አንዋ የኣለም ታላቅ ታያል በመባል የገነነች ከመሆኑ ሌላ ( ሶስተኛ ከኣለም ሃያላን ብቻታል

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ቱራኤብ - 1913) ከፍተኛ የባህር ታይል ነበረች። በዚያን ዘመን የስልጣኔ ሞኖፖሊ በም ስራቃውያን እጅ ሲሆን፣ አውሮፓውያን (አሜሪካ ገና አልተፈጠረም) የሮማና የግሪክ ስል ጣኔ ከነካቸው በስተቀር አብዛኛው ህዝብ ራቁቱን የሚሄድ በአደን የሚኖር ዘላን ዝቅተኛ ደረጃ ለይ ይገኝ የነበር፣ በጪላ ከሰሜን እስከ ደቡብ አውሮፓን የሚወሩት «ባርባርያን» የሚቸቸው ህብረተሰብ ነበሩ።

5 ከክርስትና በፊትና በጪለ ከቀይ ባህር እሰከ ኤደን ባህረ ሰላጤ ድረስ ያለው ወደብ
እስከ 7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከዚያም በጪላ በኢትዮጵያ መንግስት ቁጥጥር ስር የነበረ ወደባችን
ነው፣ ይህንንም በወቅቱ የነበሩ ግሪክና ላቲን ጸሀፊዎች በተደጋጋሚ አረጋግጠዋል (ኮንቲ ሮሲኒ ይመልከቱ)። በዘመኑ ከክርስቶስ ልደት በፊትም ሆነ በጪለ ከቀይ ባህር በስተ ምስ ራቅ ይኖር የነበረው የሳባና የሂሚያር ህዝብ፣ ከኢትዮጵያ ጋር በጎንጎ በሃይማኖትና በባህል የተሳሰረ፣ ህዝብ ነበር። በንግድ በፖለቲካና በባህር የጦር ሀይልም አንጻር የቀይ ባህር ኢትዮጵያዊነት የሚያከራክር አይደለም። ስለዚህም ቀይ ባህር ተፈራራቂ ኣለም አቀፍ ኢ ምፔሪያሊስት ታይሎች በየጊዜው የሚሰጡትን ስም (የአረብ ባህርም ተብሎ ነበር) አስወግ ደን «<u>የኢትዮጵያ ባህር</u>» ብለን ብንሰይመው ትክክለኛ ነው ብለን እንገምታለን። ይህም የ ቀይ ባህር ኢትዮጵያዊነት ኢትየጵያዊ ነን

የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ራእይና ስትራተጂ ሊሆን ይገባል።

6. እንደዚሁም ጥንታውያን ግብጾች ከአምላክ የተሰጠ በረከት ነው ብለው ያምኑ በት የነበረውና
የግብጽ ህዝበ መንግስት ከተጎጎመበት ከጥንት ዘመን ጀምሮ በፋርኦንም ዘመናት የአባይ ወንዝ 85% የኢትዮፐያን አፈርና ውሃ ከናይል ወንዝ ጋር ተቀላቅሎ በሱዳን አልፎ ግብ ጽን የሚያጥለቀለቀውና በበረሃ ለሚኖረው የግብጽ ህዝብ ብቸኛ የህይወት ምንጭ ሆኖ ሲያ ገለግል ኖርዋል፤ ባአንጻሩ ወንዛችንእስከዛሬ፣ በተለይ ዛሬ ህዝባችን በረሃብ በሚረግፍበት ወቅት ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም እንዳይውል የግብጽ መንግስት ከኣለም ኢምፔሪያሊዝም ጋር በመተባበር ዘመናዊ ኤሌትሮኒክ የጦር መሳሪያ በማግበስበስ ሳያጎርጥ ይፈታተነናል፤ ያስፈራራናል። ዛሬ ኢትዮጵያ ተንኮታኩታ ህዝች በጸረ ኢትዮጵያ ታይሎች ሸር በዘር በጎሳ ተበጣጥሳ የኢትዮጵያ ሰራዊት እስከ መጨረሻው ወታደር ድረስ መሳሪያውን ለወያኔና ለ ሻእብያ አስረክቦ በኢምፔሪያሊዝም ትብብር እንዲበታተን ስለተደረገ፣ የኢትዮጵያ ጦር ሰ ራዊት የሚባል የለንም። ይህም ሰለሆነ የአባይ ወንዛችንን ለመከላከልና ለህዝባችን ጥቅም ለማዋል ቅድሚያ ሰጥተን ህዝባችንን በአንድነት አስተባብረን የሚጠይቀውን መስዋእትነት ከፍለን፤ ጠንካራ ኢትዮጵያ መገንባት አለብን። እኛም ተመጣጣኝ ዘመናዊ የየብስና የባህ ር ጦር እንደገና መልሶ ማጎጎም ከዋናዎቹ አንዱ አጣዳፊ የፖለቲካ ኣላማችን ሊሆን ይ ገባል።

<u>ኢትዮጵያና የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከሁለተኛው የኣለም ጦርነት ወዲህ (1945-2003)</u>

7. በታሪክ የመጀመሪያው የፋርስ (ኢራን) አኬሜኒድ የተባለው ኣለም አቀ ፍ ኢምፔሪያሊዝም ከተፈጠረ ከ500 ቅድመ ክርስትያን ዘመን ጀምሮ በቀይ ባህርና በአባ ይ ወንዝ አማካኝቶ ግብጽን የወረረ የኣለም ታያላን ሁሉ የኢትዮጵያን ነጻነትና እድገት ሲፈታተን ቆይቸል። ከፋርስ ኣለም አቀፍ ኢምፔርያሊዝም በጪላ እየተፈራረቁ ከመጡት የግሪክ፣ የሮማን፣ የአረብ አስላማውያን፣የፖርቱጊዝና የኦቶማን ቱርክ፤ ብሎም የእንግሊ ዝና (ኢጣልያ) ፈረንሳይ ኢምፔርያልዝም ድቆሳ ፣በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያመለጠችበት ጊዜ የለም። የትግረው ወረራም ሆነ የግራኙ ወረራ፣ የጋዳ ጋላ ወረራም ሆነ የአ ድዋው ጦርነት የፋሽስቱ ወረራ ሁሉም የኢትዮፐያን ህልውና የተፈታተኑና ኢትዮፐያ አለ ቀላት ሲባል ፤ የኢትዮፐያ አምላክ ጥሎ አይጥለንምና፤ ወደ ህይወት የተመለሰንባቸው ና ቸው። ዛሬ ከመቼውም በበለጠ በአሜሪካን ኢምፔርያልዝም እየተደቆስን ነው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

8. ከሁለተኛው የኣለም ጦርነት በጪላ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝምን በመተካት የተጎገመው የወቅቱ የአሜሪካ ኣለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ግቡና ስትራተጂው እንደቀደሙት ሁሉ የኣለምን ህዝቦች በሙሉ በቁጥጥሩ ስር ማዋል ሰለሆነ ፤ የታይሉና የኤኮኖሚ ጥቅሙ መሰረት ለማድረግ በሚያካሂደው የጦርነት ዘመቻ የቀይ ባህር አዋሳኝ ታይል የሆነችውን ኢትዮጵያ በወጥመዱ ገብታ ከምድረ ገጽ አጥፍቶ የቀይ ባህርን ተወዳዳሪ የሌለበት የአሜሪካ ባህር ለማድረግ ከወሰነ ከአምሳ ኣመት በላይ ሆኑል። ለዚህም የሚጠቀምበት ስትራተጂ ጥንታዊት ኢትዮጵያን በጎሳ በመከፋፈልና በመበጣጠስ፣ የኢትዮጵያ የስልጣኔ ምንጭ የሆነውን ኤርትራን ከቀይ ባህር ወደባችን ጋር ለ50 ኣመት የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ሆኖ በመቆየቱ ብቻ ለብዙ ሺህ ኣመታት የቆየው ኢትዮጵያዊነቱ፣ ኢትዮጵያዊ ባህርይው ተሰርዞ ኤርትራና የቀይ ባህር ወደባችን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እጅ አዙር ቅኝ ግዛት ሆነው ከኢትዮጵያ ተገንጥለው፣ ኢትዮጵያን በመሬት የታጠረች የባህር በር የሌላት ቆማጣ አድርጉታል። ይህንን ሁኔታ አስተካክሎ የጥንታዊት የኢትዮጵያን ሙሉ አካል ማስመለስ የማያወላውል ፖለቲካ ኣላማችን ሊሆን ይገባል።

9. ኤርትራም ከተገነጠለች በጪላ ኢምፔሪያሊዝም የቀረውን የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ከፋፍሎ፤
የኢትዮጵያን መንግስት ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የሚጠቀምበት ስትራተጂ ጥንታዊት ኢትዮጵያን ትላንት እንደተመሰረቱት የአፍሪካ መንግስታት በጎሳ በመበጣጠስ ነው። ጎሳ የሰው ልጅ ከእንሰሳት የሚለይበት ከአካባቢ የተዋለዱ ቤተሰቦች የሚፈጠር፤ በጠባብ ወሰን ተለይቶ በጎንጎው በሃይማኖት ብቻውን ተለይቶ ፤ በአደንና በፍሬ ለቀማ የሚኖርበት የሰው ልጅ ወደ ስልጣኔ የሚሸጋገርበት የመጀመሪያ ደረጃ ነው። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በስንት ጥንታዊ ስልጣኔ ደረጃ የተላለፈችውን ኢትዮጵያ የብዙ ሺህ ኣመታት የስልጣኔ እድሜ ያለውን ጥንታዊው አህዳዊ ንጉሳዊ መንግስት ቅኝ ግዛቱ ለማድረግ ወስኖ፣ኢትዮጵያን የጎሳ ደሴቶች አድርጎ በአንድ በኩል እነዚህ በጎንጎ በሃይማኖትና በባህል የመለዋወጥ ባህርይ የሌላቸው ከኣለም እስከ ዘላለም በአንድ ባህርይ ተፈጥረው በአንድ በእግዚአብሄር የተሰጠ ጎንጎና ሃይማኖት ዘለለም ተወስነው የሚቀሩ ናቸው ሲለን በሌላ በኩል ለእያንዳንዱ የጎሳ ደሴት በዘፈቀደ ኒክልልኒ የሚል ስም ሰጥቶ፣ ወሰን ስጥቶ የመገንጠል መብት በ ህገ መንግ
ስት አውቆላቸው፤ ለእያንዳንዱ የጎሳ ክልል አዲስ ጎንጎ አዲስ ፊደል ሃይማኖትና ባህል ፈጥሮላቸው የኢትዮጵያዊነት ባህርያቸው ጭራሽ ተወግዶ አንዱ ከሌላው ምንም ተመሳሳይነት ሳይኖረው እንዳይነጋገርና እንዳይገናኝ ተደርጎ በረጅም ጊዜ እቅድ እርስ በእርሱ በወሰን ክርክርና ጦርነት ደም ሲፋሰስ እንዲኖር ተደርጉል።

10. እውነተኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ግን ከብዙ ሺህ ኣመታት ቀደም ብሎ ከተመሰረተ ጀምሮ የኖረው በሰላምና በጦርነት፣ በንግድ በድርቅና በረሃብ ወቅት ከቦታ ቦታ የሚዘዋወርና ብሎም የሚሰፍርና ከዚያ
ም በጋብቻ የሚደባለቅና የሚዋሀድ ህዝብ ነው። የኢትዮጵያ ጎንጎዎች ከጥንታዊ ኩሽቲክና ሴማዊ ጎንጎዎች

ጀምሮ እንደዚሁ እንደ ህዝቡ ሲደባለቁና ሲዋሃዱ ሲያድጉ ሲበለጽጉ ሲከስሙ የኖሩ ናቸው። የኢትዮጵያ ሃይማኖቶችም ከጥንታዊ የአምልኮት ሃይማኖቶች ጀምሮ ቀጥለው ከሚመሰረቱት ብሉያት (ኦ ሪ ታ ው ያ ን) ክርስትናና እስልምና ተደባልቀው ተዋህደው ነው የተፈጠረው። የኢትዮጵያ ጎንጎዎችና ፊደሎች የኢትዮጵያ ባህሎች በዚህ ኣይነት ተዋህደው ነው ኢትዮጵያዊነታችን የተፈጠረው።

11. ለዚህም ታላላቆቹ የህዝብ ፈለሳ ምስክሮች ናቸው። ከነዚህም 3ቱን ከቆላው ወደ ደጋ የፈለሱትን ህዝቦች ታሪክ ብንወስድ በ6ኛውና በ7ኛው ክፍለ ዘመን ከኤርትራ ቆላማ ሰሜን ጠረፍ ወደ ደቡብ የፈለሰውን ትግረ የከብት አርቢ ህዝብ ታሪክ ብንመለከት አክሱምን ወርሮ የአክሱም ስልጣኔ፣ የግእዝ ህዝብ ታሪክ ሲፈጸም፣ ግእዝ መነጋገሪያ ጎንጎነቱ ቀርቶ ወደ ትግራይና ትግርኛ ሲለወጥ እናያለን። በዚህም ወረራ የሳሳኒድ ፋርስኢምፔሪያልዝም እጅ እንዳለበት ይጠረጠራል። (ስለዚህ የትግረ ወረራና የአክሱም ስልጣኔ ፍጻሜ ያደረግሁት ጥናት ገና አልታተመም)። ቀጥሎም በፖርቱጊዝና የኦቶማን ቱርክ በሁለቱ የኣለም ሃያላን መሀከል የቀይ ባህርን ለመያዝ በተፈጠረው ቅራኔ፤ ግራኝ መ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ምኛ ተናጋሪው ጎሳ የሌለው እንደ ፈረንሳዩ እንደ እንግሊዙ እንደ ጀርመኑ ወደ አንድ ህዝብነት በማደግ ላይ ያለው፣ ከልዩ ልዩ ጎሳ የተውጣጣው፣ ተለይቶ የተከለለ መኖሪያ የሌለው ፣ መላው ኢትዮጵያ ሀገሩ የሆነ ኢትዮጵያዊ ነው። የምናጎቁመውም ብሄራዊ የ ፖለቲካ ስርአት - ዘር፣ ጎሳ፣ ብሄር ፣ብሄረ ሰብ፣ የማይል የማያውቅ ፣ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነጻነትና መብት ላይ የተመሰረተ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጎች በህግ ፊ ት እኩል የሆኑበት፣ የ ዲ ሞ ክ ራ ሲ ስርአት ነው።

13. የቅድመ ግራኝ የቅድመ ጋዳ ጋላ ወረራ፤ የጥንታዊት ኢትዮጵያን ወሰን ማወቅ ማረጋገጥ ከፈለጉ የፖርቲጊዝ መልክተኛ አልባሬዝ በ1520 ንጉሰ ነገስት ልብነ ድ ንግል (1508-1540) ፣ በጨላ ግራኝ ወግቶ ከዙፋን አውርዶ እስከ እለተ ሞታቸው የሚ ያሳድዳቸውን፣ ለመጎብኘት መጥቶ፣ ከቀይ ባህር በምጽዋ አድርጎ በመረብ ምላሽ (የዛሬው ኤርትራ) አድርጎ በአንጎት በአምሃራ አድርጎ መዲናቸው ዋጅ ዝዋይ አጠገብ ለመገናኘ ት በመጣበት ወቅት ስለኢትዮጵያ ድንበር ባየውና አጠያይቆ ባገኘው መረጃ መሰረት የሳ ለውን የኢትዮጵያ ካርታ ይመልከቱ። ይህና ሌላው ፖርቲጊዝ መነገደኛ ደ አልሜዳ በጨላ የሳለው ካርታ በታሪክ አዘልነታቸው ታላቅ ግምት ይሰጣቸዋል፣እዚህ ያያዝነውን የአልባሬ ዝ ካርታ አትኩረው ይመልከቱ። የቀይ ባህር ወደባችንን ያጢኑ፣የኤርትራ ወይም የኦሮም ያ ሪፐብሊክ ቢፈልጉ ቢፈልጉ አያገኙም፤ የኢትዮጵያ ታሪክ አካል አይደሉምና። በግራኝ ወረራ ዘመን (1529-1543) ከድንበር እስከ ድንበር የነበሩትን ክፍላተ ሃገር በሙሉ በመንደር ደረጃ ሳይቀር የግራኝ ታሪክ ጸሃፊ ሽሃብ አድ ዲን (አረብ ፋቂ) ዘርዝሮታል ። በመጨረሻም የገሙ ተወለጅ አባ ባህርይ በ1593 በግእዝ የተጻፈው «የጋላ ታሪክ » የተባለው በልዩ ልዩ ጎንጎ የተተረጎመው ታላቁ ትንሽ መጽሀፍ ስለ ጋላ ወረራና ስርአ ት ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋውቀናል። ( የጋላን ታሪክ እያሳታምሁ ነው።)

14. በሲ አይ ኤ የሚመራው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና በእርሱ ቁጥጥር ስር የሆኑት
የጀርመን ፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን፣ ሌሎችም የነሱ ሀገር ወለድና ባእድ ተባባሪዎች ም ሁራን ፖለቲከኛ ተብየዎች፣ ሲያሰኛቸው ኢትዮጵያ እሚባል ሀገር የለም፣ የአምታራ ፈጠ ራ ነው ይሉናል፤ ለነሱ መዘላበድ እንዲአመች የኢትዮጵያ ታሪክ ከመቶ ኣመት ከምኒልክ ዘመን አያልፍም ወዘተ ይሉናል። እውነተኛው የኢትዮጵያ ታሪክ እንዳይነገር፤ የሀገር ወ ዳዶችና አነድ ኢትዮጵያ ባዮች ድምጽ ታፍኖ፤ጥናቶቻቸው እንዳይባዙ፤ እንዳይታተሙ በስ ብሰባ እንዳይነበቡ ለህዝብ እንዳይበተኑ በልዩ ልዩ ዘዴና ሻጥር ዘግተው፤ እኛ የፈለግነው ን እንቀላምድ እየፈጠርን እናወናብድ የሚሉት በዜና ማሰራጫዎች የሚለፍፉት፣በማተሚያ ቤቶች የሚያሰራጩት ጸረ-ኢትዮጵያ ቅጥረኞች ፣ ከላይ የዘረዘርነውን የህዝባችንን ሀቀኛ ታሪክ ሁሉ ሰርዘው በኢትዮጵያ የማይተዋወቁ የማይነካኩ የጎሳ ደሴቶች ፈጥረው የኢትዮ ጵያን ህዝብ በገዝ ጎሳዎችና በተገዝ ጎሳዎች ከፋፍለው፣ የጎሳዎች ካርታ ስለው በከፋፍ ለህ ግዛ ዘዴ ኢትዮጵያን የማጥፊያ መሳሪያቸውአድርገው ከሃምሳ ኣመት ጀምሮ ኤርትራን ማስገንጠያና የባህር ወደባችንን መንጠቅያ ኦጋዴንን ማስገንጠያ ጦርነት ቀስቅሰው መሳሪያ አስታጥቀው ሲያዋጉን ሲያጋድሉን ቆይተው፣ በመጨረሻ በግንቦት 1984 ኤርትራን ሪፑብ ሊክ ብለው ወያኔን የኢትዮጵያ መንግስት ብለው፣ የኢትዮጵያ ሰራዊት አጥፍተዋል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ «ክልል» በሚሉት በታሪክ የማይታወቅ የጎሳ ደሴቶች ተበጣጥሳ፣ በወያኔ ህገ መንግስት እያንዳንዱ ክልል የራሱን መንግስት የማጎገም እስከ መገንጠል መ ብት የተሰጣቸው ናቸው፣ በአፍሪካም ሆነ በሌላው ኣለም ይህን የመሰለ ራስን ማጥፊያ ህ ገ መንግስት ያልታወቀ ከመሆኑም በላይ በተለይ በአዲሲቱ አፍሪካ እንኳን የጎሳ ፖለቲካ በህገ መንግስት የተወገዘ ነው።

15. ዛሬ ዋናው የኢምፔሪያሊዝም ስትራተጂ ከኢትዮጵያ 353 000 ኪሎ ሜት ር ካሬ ቆርጠው
(ኦነግ እስከ 600 000 ኪሎ ሜትር ካሬ ያሰፋዋል) በነኦነግ መሪነት የኦሮምያ ሬፑብሊክ ብለው ከምእራብ ጠረፍ (ወለጋ፣ ኢሊባቡር) ጀምረው በመሀል ኢትዮጵያ አልፈው አ ዲስ አበባን - የኢትዮጵያ ዋና ከተማ - በከተማነት በታሪክ የማይታወቅ ።ፊንፊኔ። ብለ ው እስከ ሀረር ጠረፍ ድረስ በምስራቅ ተዘርግተው እስከ ቦረና የኬንያ ድንበር በደቡብ ተስፋፍተው የኢምፔሪያሊዝም ቅጥረኞች፤ የወለጋ ሚሲዮናውያንና ኦነግ በታሪክ የማይታወ ቅ አካል ፈጥረዋል። የኦሮሚያ ሬፑብሊክ የኦሮምያ መሬት በታሪክየሌለ ሙሉ በሙሉ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስት የሲ. አይ ኤ የጀርመን ፕሮቴስታንት ጸረ ኢትዮጵያ ፈጠራና ዋናው የኢትዮጵያ ማጥፊያ መሳሪያ ነው። በኢምፔሪያሊስት ድጋፍ ኢትዮጵያ የአሜሪካ የእጅ ዙር ቀኝ ግዛት ሆና ወያኔና ሻእአቢያም ደርግን ተክተው በግንቦት 1983 ኣ.ም. የኢትዮጵያ መንግስት ዙፋን ላይ በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስት እጅ ከተቀመጡ በጫላ ኦነግ የኦሮምያሬፑብሊክ የተባለውን 353 000 ኪሎ ሜትር ካሬ ተረክቦ፣ በዚያ የሚገኘው ከ20 ሚሊዮን በላይ የሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ በድጋሜ ጋልኛ እንዲናገር፣ ከኦርቶዶክስ ክርስትና እንዲላቀቅ ተደርጎ ቤተክርስትያኑ ከነቄሳውስቱ ተቃጥሎ ምእመናኑ ሀገራችሁ አይደለም ተብለው እስከ ዛሬ ከአርሲ ከሀረር ከባሌ ከወለጋ በጠመንጃ እየተባረሩ ነው። የቀሩትም ጋልኛ በግድ እንዲናገሩ ተደርገው ጎንጎቸውን ትተው በትምህርት ቤት የሚማሩበት ፊደል የሚቆጥሩበት አኩሪው መታወቂያችን ጥንታዊው የማንም ጎሳ ፊደል ያልሆነው ግእዝ ፊደል ተሰርዞ በምትኩ በታሪካችን የማናውቀው የላቲን ፊደል በኢምፔሪያሊዝም ተጽእኖ ተተክቶ ኢትዮጵያውያኑ የሚኖሩት በማያውቁት የቅኝ ሀገር ነው። የግእዝንም ፊደል መልሶ በቦታው ማስቀመጥና የኢትዮጵያ ህዝብ የግሉ የብቻው አኩሪ ፊደል ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ፤ ትምህርትም የጎሳዊ ድንቁርና ማስፋፊያ መሆኑ ቀርቶ ብሄራዊ ቅርጽ ይዞ የልማት መቀየሻችን ማድረግ፤ ከፖለቲካ ፓርቲዎቻችን የምንጠብቀው የነጻነት የኢትዮጵያዊነት የአፍሪካነት እንክብካቤ ነው። እንደዚሁም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያናችንና የኢትዮጵያ እስልምና ከዋሃቢና ከሌላም ሌላም ጥቃት ተላቀው፤ ህልውናቸው ተረጋግጦ ቅዱስ ክብራቸው እንደቀድሞው ተመልሶ እንዲጎናም ማድረግ በኢትዮጵያዊነት ከሚኮሩ ፓርቲዎች በተቀዳሚነት ይጠበቃል።

16. <u>የገጠር መሬትና የገበሬው ሰቆቃ</u>

ከሰላሳ ኣመት ወዲህ ታላቁን የነጻነታችንና የስልጣኔያችን ምሰሶና ባለውለታ የሆነውን የኢትዮፕያገበሬ፤ መንግስት ነን ተብየዎቹ የደርግ ወታደራዊ አምባ ገነኖችና የወያኔ ቅጥረኞች እንደ ጃስ ተጫውተውበታል። የረጅም ጊዜ የጸረ-ኢትዮፕያ ሃይሎች እቅድ በሶሻሊስት ማርክሲስት፤ ጸረ-ጉልተኛ ካባ ለብሰው በስር ነቀል ለውጥ የሚነግዱ በመሰረቱ አድሃሪ ጎሰኛ ፖለቲካ የሚያካሂዱ፣ አምታራ ነፍጠኛ በሚሉት ከግእዝ የተወረሰው ከብዙ ጎሳ ተዋህዶ የተውጣጣው አማርኛ ተናጋሪ ክርስትያን ጥንታዊው ኢትዮፕያዊ ላይ የተነጣጠረ ጦር ነበር። ለምን ቢባል ይህን ህዝብ ከምድረ ገጽ አጥፍተው አባረው መሬቱን ለኦሮሚያ ሪፐብሊክ ለማውረስ ሲባል ነወ ከደርግ ጀምሮ በሲ አይ ኤ ረጅም እቀድ መሰረት የተወጠነው። የወያኔም ሚሽን ይከው ነው።

17. ቀይ ካባ የለበሱ እንደ ሄኖክ ክፍሌ ያሉትን የሲ አይ ኤ ቅጥረኞችና እንደ ዘገየ አሰፋው ያሉትን የኦነግ ቀነደኛ አባላት፤ የመኢሶንና ኢህአፓ መሪዎች፣ በደርግ ውስጥ የተሰገሰጉትን ጸረ-ኢትዮፕያ ዝርያዎች ምክር ተከትሎ፤ ደርግ የሀገር ወዳዱን ተራማጅ «መሬት ላራሹ» ጥሪ ገሸሽ በማድረግ፤የገጠርን መሬት የመንግስት ንብረት የሚያደርገውን አዋጅ በመጋቢት 1967 ካወጀ በጨላ መሬቱን ያጣው ጉልተኛው ብቻ ሳይሆን ጭቁኑ አራሹ ገበሬም መሬቱን ተነጥቆአል። በሚያርሰው መሬት ለይ የ መ ን ግ ስ ት ጭሰ ኛ ሆ ኖ ምንም መብት የሌለው ተደረጎ ፈላጭ ቆራጩ ባለንብረት መንግስት ብቻ ሆኑል። በዚህ መሰረት ነው ደርግ ገበሬወን ከነቤተሰቡ ከነክብቱ ነቅሎ በባርነት ወደሚያገለግልበት መንደር እንዲሰበሰብ ያደረገው። በዚህ መሰረት ነው ከደጋው በሚሊዮን ነቅሎ ፣ ሱ ዳ ን ጠ ረ ፍ አካባቢ ወስዶ ባልተዘጋጀ ቆላና በረታ ምርታቸውን እየዘረፈ ለኣመታት በኩባያ በቆሎ ያከረማቸው፤ እንዳያመልጡ በወታደር ያስጠበቃቸው፣ በበሽታ ያስጨረሳቸው። ከዘያም ደርግ ያዘጋጀለትን ወያኔ በመውረስ መሬት የመንግስትንብረት ሆኖ ቀጥሎ የገበሬውም ሰቆቃ ተባብሰዋል። እስከ ዛሬ አማርኛ ተናጋሪው ከርስትያን ገበሬ ከአሩሲ ከሀረር ከወለጋ ወዘተ ጨጎኝ ነፍጠኛ ሀገርህ ሂድ እየተባለ እየተነቀለ እየተጋዘ ነው። ከጎጃም ከጎንደር ከወሎ ከሸዋ በነቂስ እየተለቀመ የደርግ ተባባሪ እየተባለ መሬቱ ተነጥቆ ለወያኔ ደጋፊዎች ይከፋፈላል። አቤት ባዩ ገበሬ እስከ አዲስ አበባ ቢመላለስም ሰሚ አላገኘም። ኢትዮፕያዊ ነኝ የሚል የፖለቲካ ፓርቲ ሁሉ የመሬት ባለንብረትነትን ለገበሬው አስጨብጦ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የሚፈራረቅበትን መንግስታዊ ግፍ ፍጻሜ ማድረስ አለበት። የዚህም መፍቻው በፕሮግራማችሁ እንደሚነበበው መሬትን የግል ንብረት ማድረግ ነው። የወያኔ አዲስ የዶላር ሚለዮኔሮች መሬቱነ በግዚ ከገበሬው አንዳይ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ነጥቁት ከተፈለገ የጥንቱን *ah%* የቤተሰብ የጋርዮሽ ንበረት ስርኣት መልሶ በጥናት ማጎጎም ነው። ቢሆንም እንዱስትሪዎች ስያድጉ የንግድ እርሻዎች ሲስፋፋ ከተሞች ስያድጉ የገጠሩ እርሻ መጠንና የገበሬው ቁጥር መቀነሱ አይቀርም።

<u>ምን ማድረግ አለብን ?</u>

18. የኔ አጎም ወያኔና ሻእብያ የኢትዮፕያን መንግስት ስልጣን ከጨበጡበት ከግንቦት 1983 ወዲህ ኢትዮፕያ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻነትዋን አጥታ የአሜሪካን የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ሆናለች የሚል ነው። እዚህም አጎም ላይ የደረስኩት ሻእብያና ወያኔ በሲ አይ ኤ የተፈጠሩ ቅጥረኛ ድርጅቶች መሆናቸው ላይ በመመርኮዝ፤የዋሽንግተን የአፍሪካ ፖሊሲ በተለይ የአፍሪካ ቀንድን በሚመለከት ታዛዝ ጉዳይ አስፈጻሚ መሆናቸውን በማየት፤ የኢትዮፕያ ወታደር ደም የአሜሪካ ቅጥረኛ ሆኖ የአሜሪካን ኣለም አቀፍ ሃይልና ጥቅም ለማስከበር ሲፈስበማየት፣ ይህ በተደጋጋሚ በሩዋንዳ በዛይር በሱዳን፤ በተለይ ደግሞ በተደጋጋሚ በሱማሌ ታይቸል። ሻእብያና ወያኔ በሚያካሂዱት የነጻነትና የሰብኣዊ መብት ረገጣ አሜሪካ ስለሚተባበራቸው ፤ ስለ ኢትዮፕያ ጥቅም ወይም ችግር ግድ የሌላቸው ከመሆኑም በላይ በሲ አይ ኤ ረጅም ጊዜ እቅድ መሰረት ኢትዮፕያንና ኢትዮፕያዊነትን ለማጥፋት ቆርጠው የተነሱ መሆናቸውን በመገንዘብ ፤ በቅርብ እንደተባለው የጠላት መንግስት በመሆናቸው፣ በአጠቃላይ አሜሪካ እንደፈለገ ጥቅሙን ለማስከበር ስለሚያዛቸው ነው። እንደአሁን ደግሞ ኢትዮፕያ በድህነት ላይ ድርቅ አይሉት ድርቅ እየተፈራረቀባት 15 ሚሊዮን በረሀብ እየረገፈ ነው.። በኤድስ በሽታ በሚሊዮን እየረገፈ፤ አልታይ ብቸቸው የአሜሪካኑ የጦር አዛዝ ጄኔራ ል ፍ ራ ን ክ ስ አዲስ አበባ መጥተው (ሰኔ መጨረሻ ላይ) ኢትዮፕያውያን በአሜሪካ ኢምፔርያልዝም ላይ የተነሳውን ሽብርተኛነት (ተረርሪዝም) እየተዋጋን በደማችን በህይወታችን እንድንከፍል በድጋሚ ጋብዘውናል። በእኛ አሰተያየት አሜሪካኖች ሽብርተኛነት (ተሬርሪዝም) የሚሉት በርግጥ ተቃዋሚዎቹን ሀሉ አሸባሪ ብሎ መደምሰስ ማስገበር የሚፈልግ ኣለምን ሊገዛ የተነሳ ኢምፔሪያሊስት ታያል መንግስት ችግር ሊሆን ይችላል። ኢትዮፕያ ግን ከኣለም ድሆች የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘች፤ እንዴት በአጥንቱ ራቁቱን የሚሄደው ህዝብ በተጨማሪ ሽብርተኛነት (ተሬርሪዝም) አየተዋጋህ ሙት ይባላል? ሽብርተኛነት (ተሬርሪዝም) የኢትዮፕያ ተቀዳሚ ችግር ነው ተብሎ? ይህስ ራሱ የነጻነት ማጣት ማረጋገጫ አይደለም ወይ? ዛሬም እጃችንን ወደ እግዚአብሄር ዘርግተን ያለምንም በደል አሜሪካ የሚያደርሰብንን ግፍ እንዲያርቅልን እንጸልያለን። ኣጼ ታይለ ስላሴ እንዳሉት የኢትዮፕያ ጉዳይ የእግዚአብሄር ምስጢር ነው።

19. በዚህ ኣይነት ዛሬ የኣለም አቀፍ ኢምፔርያልዝም እጅ አዙር ቅኝ ግዛት መሆናችን ነጻነት ማጣታችን
ተቀዳሚ ችግራችን ስለሆነ መልሰን ነጻነታችንን መጨበጥ ተቀዳሚ ኣላማችን ሊሆን ይገባል። ለዚህ የሚገባውን ፖለቲካ መተለም ኢትዮፕያዊ ነን አንሽጥም አነለወጥም የሚሉ ፓርቲዎቻችንን ጭንቅላት የሚያናውጽ
ትልቅ ፕሮብሌም ነው። ስለዚህ ነጻነታችንን አሰከብረን የሙሉ አካላችን ማረጋገጫ ወደባችንን፤ አባይ ወንዛች
ንን አሰከብረን ፤ ልእልናችንን አሰከብረን ፤ የከፋፍለህ ግዛ መሳሪያ እንዳይሆን አነድነታችንን አሰከብረን ሃይማኖታችንን ጎንጎችንን ፊደላችንን ባህላችንን ማንነታችንን ኢትዮፕያዊነታችንን አሰከብረን፤
ከኣለም አቀፍ ኢምፔርያልዝም ጋር ተከባብሮ ለመኖር የሚያስችለን ፖለቲካ መቀየስ ይኖርብናል።
ጥያቄው ይህ ኣይነት ፖለቲካ ሊኖር ይችላል ወይ ሳይሆን፤ ፓርቲዎቻችን በአንድነት፣ ግራ ቀኝ ሳይባል፣ ግልጽየሆነ ፖለቲካ ነድፈው፣ እስከ ዛሬ የቆየውን የድብቅ ከመሬት ስር ተቀብሮ ሚስጢር በመሆን የጥቂቶች ሞኖፓሊ፣ እንጃን ህዝብ የፓርቲ አባሎች ሳያውቁት፣ሃገራችንን ሲቦረቡር የቆየውን የውጭ ፖለቲካ ዘይቤ አስወግዶ፤ ነጻነታችንን ህልውናችንን የሚመለከት በመሆኑ ህዝብ ያወቀው ህዝብ የተወያየበት ፖለቲካ ሊሆን ይገባል።
20. በተጨባጭ ምን ማድረግ አለብን የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እስካሁን ከዘረዘርጃቸው በተጨማሪ አንዳንድ ሃሳብ ለማከል ያህል ህልውናችንንና ነጻነታችንን ለማስከብር የመጀመሪያው እርምጃ ደህንናታችንን ማስከበር ነው። ይህንንም ለማድረግ በል

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እልናችና በነጻነት መብታችን በመጠቀም በጣም የተጎዳን ድሃ ሀገር በመሆናችን ጨ.ያላን
መንግስታት ሲሆን በፈቃዳቸው አሰተያየት አርገው አቅማችንን መልሰን እስከምንገነባ ጉ
ልበታችን እስከሚበረታ ድረስ ለተወሰነ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን ከማድረግ እንዲቆጠቡ
መጠየቅ። ይ ህንንም ሞ ራቶሪየም ብየዋለሁ። እኔ ለጊዜው ስት ሞ ራቶሪየም የምንጠይ
ቅባቸው መሰኮች እንደሚከተሉት አቅርቤያለሁ። ጉዳዩ ሰፊ ዲሞ ክራቲክ ውይይት በውስጣ
ችን የሚጠይቅ ነው ።

1. አንደኛ ሞ ራቶሪየም፤ በማናቸውም ኣይነት የስለላ ተግባር። ይህ በተለይ የአሜሪካ
ኑን ሲ. አ ይ. ኤ የሚመለከት ሲሆን በተጨማሪ የምእራባውያንን – የእንግሊዙን ኤም
አይ 5. የጀርመኑን, የሆላንዱን, የስዊድኑን ካናዳውን አውስትራልያውያን የፈረንሳዩንና የ
እስራኤሉን ሞ ሳድ ያጠቃልላል። እነዚህ ሃያላን በአፍሪካ በእስያ ወይም ላቲን አሜሪካን
ዲፐሎማቶች፣ በኣለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ወይም ግለሰቦች አማካይነትም ሆነ በሃገር ውስ
ጥ ባንዳ ዜጎችና ቅጥረኞች አማካይነት የእጅ አዙር ስለላም በዚሁ ውስጥ ይጠቃለላል።

በእውነቱ ከሆነ ፤ እኛ በጨ.ላ ቀርነታችን ሳንገነዘበው ፤ ደህንነታችንን
አሳልፈን እንሰጥ የነበረው በ19 መቶ ክፍለ ዘመን ጀ ም ሮ ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ
ከሁለቱ የኣለም ተቃራኒ ኢምፔርያልስት ሀገሮች ጋር በተለይ በቴዎድሮስ (1855–1868)
ዘመን የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ ነበር። ከዚያን ጊ
ዜ ጀምሮ በዲፕሎማቲክ መልክተኛ መልክ , በሃይማኖት ሚሰዮኔር መልክ የሚመጣው፣
ቴዎድሮስ በጨ.ላ አሉ እንደሚ ባለው፣ በሌላው አፍሪካ ቅኝ ግዛት እንደሆነው ሁሉ፣
በአንድ እጁ መጽሀፍ ቅዱሰ በሌላ እጁ ጠመንጃይዞ በሰላይነት የሚያገለግለው ቁጥር
ውስጥ አይገባም ነበር.። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመንግስት መልክተኞች ተብለው የሚ
መጡ ወይም ሚስዮናውያን አነድ ሁለት ልጆች ወደ ሃገራቸው ወስደው 6 ወ ር 1
ኣመት ከቆዩ በጨ.ላ ሀገር ቤት ተመልሰው ፈረንሳይ ወይም እንግሊዝ ሆንን ሰለጠንን
ብለው በጠራራ ጸሀይ ሱፍ ለብሰው ክራባት አስረው ጫማ አድርገው አነዳንዴም ሸ
ማ ለብሶ በባዶ እግሩ የሚሄደውን ወገናቸውን በንቀት እያዩ መጃንንቱን እየተሳደቡ ጅራ
ፍ የቀመሱም ነበሩ። ከነዚህ ብዙዎች. ሀገራ ቸውን በቅንንነት ያገለገሉ ሲገኙበት ሌሎ
ች ተመልሰው ከሚስዮንም ጋር ተያይዘው ሆነ ለብቻቸው የሚቀጥራቸውን የወጭ ተወላ
ጅ ጌታቸውን በአስተርጉሚነትና በሰላይነት አገልግለዋል። ፈረንጁም ሆነ ሀገር ወለዱ
ሰላይ የንጉሱን ጠባይ ወዳጅና ጠላት የ ጦር ታይል ወዘተ እየሰለሉ ሪፖርት
የሚያቀርቡ እነዚህ ናቸው። ይህም መረጃ እንደአስፈላጊነቱ ይውላል። በዚህ ኣይነት ስ
ለሃገራችን እንግሊዝ መዝገበ ታሪክ ውስጥ ከኢንተሊጀንስ ሪፖርት የምናገኘው መረ
ጃ መሬት የሚወድቅ አይደለም.። እንግሊዘም በ 1868 የቴዎድሮስን ጦር ከፋፍሎ ያለ
አንዳች ጦርነት መግደላ ድረስ መዝመት የቻለው በስለላ ወጤት ጭምር ነው ቢባል ሀሰ
ት አይሆንም.። በተለይ በእንግሊዝ ጋብዝነት በዋና ጠላትነት ቀይ ባህርን እንዲይዝ የተደ
ረገው ጣሊያን፣ በመጃንንቱም መሃል ሆነ በተራው ህዝብ መሃል ፣ሰላይ መመልመል ስ
ራዬ ብለው የተያያዘው ጉዳይ ነበ ር። « ት ራ ዱ ቶ ሬ» (አስተርጉሚ) ወይም «ት
ራ ዲ ቶ ሬ» ሀገሩ ን ከዳተኛ ተብለው የተተረተባ ቸ ው የውጫሌው ስምምነት
ቱርጁማን
ግራዝማች ዮሴፍ ብቻ አልነበሩም። በተለይ ጣሊያን ኤርትራን ከያዘች በጨ.ላ ሳር ቅ
ጠሉ « ኢ ን ፎ ር ማቶ ሪ» ነ በ ር። መረብን እየተሻገረ ኢትዮፕያን ከዳር እሰ
ከ ዳር የሚሰልል። ከብዛቱ የተነሳ በሃገራችንም ለሰላይ የተሰጠው የመጀመሪያው ስም
«ኢ ን ፎ ር ማ ቶ ሪ» ወይም ባጭሩ « ፊርማቶሪ» ነበር። በኣጼ ምኒልክ ዘመነ
መንግስት የስለላ አገልግሎት፤ ዛሬ ደህንነት የምንለው ተጀምሮ በኣድዋ ጦርነት ጊዜ አ
ስተዋጽኦ እንዳደረገ ይነገራል። የኤርትራ ገዝ የነበረው ፌርዲናንዶ ማርቲኒ (1897–1907)
የቀን በቀን ማስታወሻውን (ዳ ያ ሪ) አጠራቅሞ ባዘጋጀው አራት ቅጽ የወጣው ተላቅ
የታሪክ መጽሀፍ ውስጥ በየገጹ የሚያቀርበው በየአቅጣጫው የሚልካቸው ኢ ን ፎ ር
ማ ቶ ሪ ዎች የሚሰጡትን ሪፖርት ነበር። የሪፖርቱ ፋይዳ ከአንዱ ወደ ሌላው መለ
ያየቱ አያስደንቅም። በ ፋ ሽ ስ ት ም የወረራ ዘመን (1936–1941) የአርበኞቻችንን
ኮቴ በመከታተል የኢ ን ፎ ር ማ ቶ ሪ ው ሚና ተመሳሳይ ነበር። በአርበኞቹ ሲያዝም
አይቀጡ ቅጣት ነበር የሚጠብቀው። .

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ወደ ቀዳማዊ ታይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ስንደርስ የደህንነቱ ስራ የወቅቱ ኣለ
ም አቀፍ ታያል ሚና ሆኖ በቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ወዳጅ ብለው ያቀረቡት የአሜሪካ
ና የእስራኤል ሞሳድ ሃላፊነት እንደሆነ ተደርጎ ነጻ አጎም ሳይኖረን፤ የደህንነታችን
ፖሊሲ የሚነደፈው ከነዚህ ጋር በአንድነት ተቀምጦ ይመስላል.። ኣንድ የንጉሱ ካቢኔ ጀነ
ራል በቅርቡ እንደነገሩን ፖል ሄንዜ አብቼቸው የደህንነት ጉዳ ሰው ነበር ብለዋል። በ
ዚያው መጠን ከሀገር ውስጥ ፤ ኤርትራና ትግራይን ጨምሮ ፣የሚመለመለው የባንዳ ቅ
ጥረኛ ቁጥር ከፋሽሰቱኢንፎርማቶሪ አያንስም ነበር ቢባል ሲልቢያ ፓንክረስት ቤት ያደገ
ው ኢትዮፕያዊነትን የማያውቀው ቀንደኛ
«ት ራ ዲ ቶ ሬ» እንድርያስና ግብረ አበሩ አብዱል መሀመድ አባ ቦራ አይክዱም።።
ስለሁሉም ኮሎኔል ተሰፋዬ ብዙ ሊነግሩን ይችላሉ። እንዴት ፖል ሄንዜ በ «ማርክሲሰ
ቱ» መንግስት እየተጋበዘ እኛንው በዘር በጎንጎለመከፋፈል እንዲረዳው የኢትዮፕያን ገጠር
ከዳር እስከ ዳር አጥንቶ ካርታ አንዲሰበስብ ተደረገ? ይህ ማለት ሀገራችን ለሙሶሊኒ
የራስዋን መረጃ ታካፍል ነበር እንደማለት ነው። ይህ ማለት የኢምፔሪያሊስት ጠላታ
ችን በአንድ በኩል ከኛ ጋር ተቀምጦ ሚስጢር ተካፋይ ሆኖ ገበናችንን እንዲያውቅ ሲደረ
ግ በሌላ በኩል ጠላቶቻችንን እነሻእብያን ወያኔን አደራጅቶ, መሳሪያ አስ ታጥቆ ምግባ
ቸውን አቅርቦ ጦርነት እንዲከፍቱብን ያደርጋል ፤ በጦር ሜዳ እየተክታተለ በሳቴላይት
መረጃ እየሰጠ ሰራዊታችንን ያሰጨርሳል። ይህ ነው የኢትዮፕያ ደህንነት። የዛሬው የጠ
ላት ግዛት ዘመን የዚህ አሰራር ውጤት ነው። ስለዚህ ነው የደህንነት ጉዳይ የኛ አለኝ
ታ ለሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንገብጋቢ የሚሆነው።

2. ሁለተኛ ሞራቶሪየም ፤ የውጭ ሚስዮናውያን ድርጅቶችን መዝጋት፣ መከተል ያለብን
ብሄራዊ የትምህርትናየባህ ል ፖሊሲ፣ በጥንታዊ ኢትዮፕያዊነትና በግእዝ፣ በኦርቶዶክስ
ክርስትያን ጥንታዊ መጻህፍትና በኢትዮፕያ እስልምና ላይ፣ ባ ጠ ቃ ላ ይ በኢትዮፕ
ያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ እንጂ በምእራባውያን «ስልጣኔ»ላይ ያልተመሰረተ በ
መሆኑ፤ (ከዚህ በታች በትምህርትና ባህል ምእራፍ ይመልከቱ) ካለፈው ልምድ የተማርነው
እንደሚመክረን እንቅፋት ሊሆኑ ስለሚችል ጠንካራ መሰረት እስኪኖረን ድረስ የውጭ
የክርስትያን ሚስዮናውያን ድርጅቶችም ሆነ ዋሃቢ እስላማውያንና ሌሎቹም በገንዘብ ሃይ
ል የውጭ ሃይማኖት የሚያስፋፉትን ጨምሮ መዝጋት፤ ዛሬ በሀገር ውስጥ የሚገኙት
ኢትዮፕያዊ ካቶሊካውያንና ፕሮቴስታንት አማኒዎች የሃይማኖት ነጻነት እንደተከበረ ሆ
ኖ፤

3. ሶስተኛ ሞራቶሪየም፣ የጦ ር መሳሪያ ንግድ ከመንግስት ውጭ፣ ለውጭ መንግስ
ት ወይም ኩባንያዎች ያደሩ ቅጥረኞች ወታደሮች መመልመል ማሰልጠን በኢትዮፕያ ም
ድር፣ የኢትዮፕያ ጦር በምንም ምክንያት ለ ለውጭ መንግስት ወይም ኩባንያ በቅጥረኝ
ነት ለውጊያ አንዳይላክ፣ እንደዚሁም የኢትዮፕያ መንግስት
ለውጭ ሃያላን በወታደራዊ ቤዝነትም ሆነ፤ እስር ቤት፤ ወይም በሌላ መንገድ እንዲያ
ገለግል ቅንጣት
መሬት በኮንትራትም ሆነ በሌላ ኣይነት ውል ወይም ስምምነት እንዳይሰጥ።

4, <u>አንዱ የረሃባችን መፍትሄ፣ በአርቲፊስየል ኢንጅነሪንግ የሚመረቱ ሰብሎች (ጂ.ኤ ም.
ኦ) ኢትዮፕያ እንዳይገቡና በኢትዮያ ጥንታዊ አዝርእት ላይ የሚካሄደው ጀነቲክ አርቲ
ፊሲየል ኢንጅነሪንግና ዘረፋ በ ሞ ራ ቶ ሪ የ ም እንዲታገድ፣</u>

ለምን ረሃብ የኢትዮፕያ መታወቂያና መጠሪያ ሆነ? ከጥቂት ኣመታት .
ጀምሮ የሀገር ውስጥና የውጭ ኤክሰፐርቶች በኢትዮፕያ የሚደጋገመውና አልቆም ያለ
ው ረሃብ፣ እነፕሮፌሰር መስፍን እንደሚሉት የተፈጥሮ እርግማን ወይም የመንግስት ብቃ
ት ማጣት ብቻ ሳይሆን ፣ የኢትዮፕያ ረሃብ አንዱ ምክንያት እስከዛሬ የኢትዮፕያ ገበ
ሬ በብዙ ሺህ ኣመታት የእርሻ ባህሉና ልምድ ተንከባክቦ ያቆየውን የሰብሎች ተመሳ
ሳይ እማይገኝለት ሀብት (ጀ ነ ቲ ክ ዳ ይ በ ር ሲ ቲ ) የምእራባውያን በተለይ
የአሜሪካ በአርቲፊስየል ጀኔቲክኢንጂነሪንግ የተመረቱ ( ጀ ኤም ኦ)፣ በአውሮፖ የተከ
ለከሉ፣ ለኢትዮፕያ መሬትና አየር (ኤኮሎጂ) የማይሰማሙ፣ ለጤናና ለምርት ጠንቅ የሆ
ኑ ሰብሎች፣ለኣመታት በተለይ በአሁኑ በወያኔ መንግስት ትብብርና ከትርፋ ተካፋይነት፣ (
የጀርመኑ የርዳታ ኤክስፐርት ቲለማን ኤሊየሰን እንደሚያረጋግጥልን) መጣያ ( ዳ ም ፒ
ን ግ ግራ ው ንድ ) ስለሆነች ነው ይሉናል። ይህንን ኣይነት ሰብሎች በማምረትና ለኣ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ለም ድሆች በመሸጥ የታወቁት ታላላቅ ኩባንያዎች አሜሪካኖች ከመሆናቸው ሌላ ያለ ሶስ ተ ኛው ኣለም ሌላ ገብያ የላቸውም። በዚህ ሰሞ ንምአሜሪካ እነዚሁኑ ሰብሎች በብዛት ፥ እርዳታ በሚሉት ሽያጭ ስም እንደገና ልካለች። ከሀገራችን ምሁራን በዚህ መስክ አ ጥብቀው ከሚታገሉት አርበኞቻችን ውስጥ ዶክተር መላኩ ወረደና ኦታዋ ( ካናዳ ) ያለው ዶክተር አውጋቸው ተሾመ መጠቀስ ይገባቸዋል። በኣለም እውቅና ያገኘውና ለብዙ አፍሪካ ሀገሮች ፥«የመኖር አለመኖር ወሳኝ ሰብሎች» (ሲድስ ኦፍ ሰርባይባል) በተባለ ፕ ሮጀክት አማካሪ ሆኖ የሚያገለግለው ዶክተር መላኩ ወረደ አዲስ አበባ የራሱን «የአዝር እት ዘር ሀብት ጥበቃ ማእከል» እያካሄደናየጥንታዊ ኢትዮጵያገበሬ ያካበተውን የዘር ኣይነቶች (ላንድ ሬስ) ሀብታችንን በአንድ ቦታ እየሰበሰበ በመንከባከብ ላይ ይገኛል። ዶ ክተር መላኩ ከጦብያ ጋዜጣ ጋር ባደረገው ውይይት እንዲህ ብቸል-

> «የኢትዮፕያን ጥንታዊ የአዝርእት ሀብት በመንከባከብና በነዚህም በመጠቀም የ እርሻ ምርታችንን
> ከፍ አድርገን በተከታታይ ከሚፈጀን ረሃብ መላቀቅ መቻል አለብን። የአዝርእት ሀብታችን የምግባ ችን ምንጭ ነው። ስለዚህም ኢትዮፕያን እንደ ጥንቱ መልሰን የጥጋብና የደስታ ሀገር ማድረ ግ ኣማንችልበት ምክንያት የለም። የኢትዮፕያ የእርሻ ስልጣኔ የብዙ ሺህ ኣመታት እድሜ ያለው ነው። የኢትዮፕያ ገበሬ ም ይህ ነው የማይባል የእርሻ ስልጣኔና ልምድ አዝሎ የሚኖር ባለአደራችን በመሆኑ በዚህ ከትውልድ ትውልድ የተላለፈልን ልምድ በመጠቀም ምርታችንን ማ ሳደግ መቻል አለ ብን። እስከዛሬ ያ ታላቁ ሀብታችንና መመኪያችን ሊሆን የሚ ገባው የገበሬያችን እጅግ ከፍተኛ የእ ርሻ ልምድና እውቀት ተንቆና፣ ገበሬው ደንቆሮና ዋጋ ቢስ ሆኖ በመቆጠሩ፣ የእኛ አማካሪዎችና
> አሰተማሪዎችም የራሳችንን ትተን በምትኩ የምእራባውያንን የእርሻ ዘዴና ቴክኖሎ ጂ እንድንከተል
> አድርገውናል። ይህም ስለሆነ የኢትዮፕያ የእርሻ ፖሊሲ ከላይ እስከታች ከታች አስከ ላይ እንደገናመጠናት ይኖርበታል። ... በዚህ ኣይነት ከጥቂት ኣመታት ወዲ ህ በምእራባውያን በአርቲፊስየል ኢንጂነሪንግ የተመረቱ ሰብሎች (ጂ ኤም ኦ) ወረራ ና የኢትዮፕያ ኣዝርእትም ለዘመናት አዝለው የኖሩትን ጂን በመለዋወጥ የተፈጥሮ ጤናማ እድገታቸውን ከማጨናገፋቸውም በላይ በእርሻ ምርትም ላ ይ ኣጥፊ ሚናቸው ግልጽ ነው።»

ከውጭ ምሁራን መሀል ይህንን የአዝርእት አርቲፊሲየል ኢንጂነሪንግ (ጂ .ኤ ም. ኦ) ጠንቅ የምርምር ግኝት ከሚመዐሩት ዋናው የካናዳው ኦታዋ ዩኒበርስቲ ተመራማሪ የሆኑት ፐሮፌሰር ሚሼል ኩሱዶብስኪ ናቸው። ይህንንም ፥«የረሀብን ዘር በኢትዮፕያ መዝራት»» ፥ በተባለው ጽሁፋቸው በሰፊ ው አስረድተዋል። (ዘ ኤ ኮ ሎ ጂ ስ ት፣ መ ስ ከ ረ ም 2000) ። የካናዳው ፕ ሮፌሰር የሚያተኩሩት በሶስተኛው ኣለም ሀገሮ ች በተለይ አፍሪካ በተለይ ኢትዮፕያ በ ዚሁ በአርቲፊስየል ኢንጂነሪንግ የተመረቱ ምርቶች ( በተለይ በቆሎ) በእርዳታ ስም ተጥ ለቅልቀው ጥንታዊ ብሄራዊ አዝርእትን ( ገብስ ስንዴ ጤፍ አተር ማሽላ ቡና ወዘተ ) በአርቲፊስየል ኢንጅነሪንግ ተደምሰሰው እንደምን ከረሃብ መላቀቅ እንዳቃታቸው ነው። ለዚህም ረሃብና በእርዳታ ስም ንግድ የኣለም ባንክ፣ የኣለም የገንዘብ ፈንድና ( ኢንተ ርናሽናል ሞ ነተሪ ፈንድ) እና የኣለም ንግድ ድርጅት በነጻ ገብያዘመቻ ስም (ሰትራክቸራ ል አድጀስትመንት ፣ ዲሬጉሌሽን ወ ዘ ተ) ብሄራዊ የእርሻ ፕሮግራሞችንማሰረዝ፣የእ ህል ጎተራዎችን ማዘጋት ፣ የአዝርእት ባንኮችን ማዘጋት፣ ኤክስቴንሽ አገልግሎትና ብ ድርና ማ ናቸውም የመንግስት እርዳታ ማስቆም ጥቂቶቹ ናቸው። (የአሜሪካ መንግስትና የምእራብ አውሮፓ መንግስታት ለገበሬዎቻቸው የሚሰጡት ከፍተኛ ድጎማ እንዳለ ሆኖ!)፣ በ አጠቃላይ የኢትዮፕያ መንግስት ተብየው ን እርሻ ፖሊሲ የሚያወጡት እነዚሁ ኣለ ም አቀፍ ድርጅቶች ከዋሽንግተን -እየላኩ ነው። ከዚሁ በእርዳታ ስም ከሚሸጠውጂ ኤ ም ኦ እህል ጋር አብሮ በነዚሁ የአሜሪካን ኩባንያዎች (አርቸር ዳንኤልስ ሚድ ላን ድ፣ ፓዮኒየር ሃይ ብሬድ ኢንተርናሽናል፣ ካርጊል ኢ ን ኮ ወ ዘ ተ) በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጥ ማዳበሪያ ገበሬው እንዲገዛይገደዳል። ከሁሉም የሚያስገርመው በደል እንደ ኩሱ ዶብስኪ አባባል የኛንው ጥንታዊ ሰብል በአርቲፊስየል ኢንጅነሪንግ ለውጠው የፔተንት ባለቤት በመሆን ለኛው ለራሳችን ለሌሎችም ሸጠው አትራፊዎች መሆናቸው ነው! የየጤ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ፋችንም በፔተንቱ ባለቤት ኩባንያ አትራፊነት አሜሪካ ተመርቶ ተመል ሶ ቢሸጥልን ል ንደነቅ አይገባም። በዚህ ኣይነት የአሜሪካ ኩባንያዎች በአንድ በኩል የኢትዮፕያን ጥን ታዊ የተለየ ተፈላጊ ጂንስ ያቸቸውን ኣዝርእት (ላንድ ሬስሰ) በህገ ወጥ መንገድ በመስ ረቅና ባለቤት በመሆን በዚህ ኣይነት የኢትዮፕያ ገበሬ ጥንታዊ ብሄራዊ ሰብሎቹን እየተነ ጠቀና ባህላዊ የእርሻ ዘዴና ቴክኖሎጂ ( ኦርጋኒክ እርሻ ዘዴ) እየተወ በግድ የአሜሪካ ኩባንያዎች በእርዳታ ስም የሚሸጡለትን የአርቲፊሲየል ሰብሎች አምራችና በላተኛ መደረ ጉ ለመቸውም መቆሚያ የሌለው የረሃብ ሰንሰለት መዳረጉ ነው፣ ይላሉ ኮሱዶብስኪ ሲ ደመድም።

በአንጻሩ የረሃብተኛዋ ኢትዮፕያ አዝርእት (ስ ን ዴ ገ ብ ስ ጤ ፍ ማሽላ ቡና ) የበለጸገውን አሜሪካን የምግብ ሰብሎች ከበሽታ ተከላክለው ከፍተኛ ምር ት እያስገኙ ነው። አዘውትሮ የሚጠቀሰው የካሊፎርኒያው (ሳ ሜ ሪ ካ ዊ) ገብስ በብጫ ድንክዬ ባይረሰ እየተመታ ምርቱ ስላሽቆለቆለ ባይረሱን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ወጭ በማስፈለጉ ፣ ከኢትዮፕያ ገብስ «ጀርም ፕላዝማ» ተወስዶ በአርትፊሲየል ኢንጀሪንገ ከካሊፎርኒያወ ገብስ ጋር ተዋህዶ ሲዘራ ባይረሱን መከላከል ስለቻለ ቅድሞ ለድንክዬው ባይረሰ ቁጥጥር ያወጡ የነበረውን 160 ሚሊዮን ዶላር አድኖላቸዋል ተብ ቸል። እንደ ዶክተር አውጋቸው አባባል ከሆነ በኢትዮፕያ ገብስላይ በተደረገው አርቲፊ ስየል ኢንጀነሪንግ ተጠቃሚ የሆነው ካሊፎርኒያ ብቻ ሳይሆን አሜሪካ በሙሉ፣ እንዲሁ ም ካናዳ፣ አውስትራልያና ሌሎችም ብዙ ሀገሮች ሲሆኑ ለባይረሱ ያወጡ የነበረውና አሁን ያዳኑት አጠቃላይ ወጭ እስከ 600 ሚሊየን ዶላር እንደሚገመት ያረጋግጣል። ከላ ይ እንዳልነው ለዚህ ትርፍ መከፈል የነበረ በት የኢትዮፕያ ገበሬ ሲሆን በተጨባጭ ግ ን በ ዘፈቀደ በኢትዮፕያ ገብስ ፔ ተ ን ት እያወጠ የሚነ ግ ደውና የሚዘርፈው የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ የሆነው ኤጀንት ነው። በተጨማ ሪ ሌላው የኢትዮፕያ ባዮ ዲበርሲቲ ማእከል ሃላፊ የሆነው አበበ ደምሴ በልዩ ልዩ መንገድ በኢትዮፕያ አዝ ርእት አርትፊስየል እንጅነሪንግተጠቃሚዎች ውሰጥ የምእራብ አውሮፓና ጃፓን እንደሚገ ኙበት አረጋግኘል።

ተደጋግሞ እንደ ተነገረውና በተጨባጭም በመስክ ምርምር እንደታየው የ ረሃቡ መፍትሄ ገበሬው እንደ ጥንቱ ነጻነቱን ጨብጦ ጥንታዊ አዝርእት ከዝርፊያና ከአ ርቲፊሲየል የጂንስ ለውጥ ተጠብቀው በእርዳታ ስም ከሚያጥለቀልቁን ጂ. ኤ ም. ኦ ሰብሎች ላይ ሞ ራ ቶ ሪ የ ም ተደንግጎ በሰላም ባህላዊውን ኦርጋኒክኦርጋኒክ የእ ርሻ ዘዴ በራሱ ቴክኖሎጂ እንደገና መልሶ በስራ ለይ ሲያውልና በመንግስት እየተረዳ በሳይንሳዊ ምርምር እየተረዳ በኤኮኖሚ ፖሊሲ ምርጫችን ውስጥ የኢምፔሪያሊዝም ሆነ የነሱ በነጻ ገብያ ስም በርዳታ ስም ድንበር እየዘለሉ ከሚገቡ ኣለም አቀፍ ድርጅ ቶች ነጻ ሆኖ የራሱን ተጨባጭ የተፈጥሮ እድገት ሚዛን ሲይዝ ብቻ ነው። የመስፍና ው ( ሰሜን ወ ሎ) ገበሬ አበለ ዘውዱ ቀድሞ ይጠቀምባቸው የነበሩትን ከውጭ የሚመጡ በከፍተኛ ዋጋ የሚገዛቸውን ማዳበሪያና ጸረ ተባይ መርዝ ( ብዙጊዜ አ ው ሮ ፓ ና አ ሜ ሪ ካ የተከለከለ በእርሻና በሰብል ላይ ጉዳት ማድ ረ ሱ የታ ወቀ ) አሰወግዶ በኦርጋኒክ ማዳበሪያና በሀገር ውስጥ በሚመረት ከጥንት ሲያያዝ የመ ጣ የተባይ መከላከያ ዘዴ በመጠቀም ምርቱን እንዳሳደገና በውጭ አክሰፐርቶች ጭም ር አድናቆት እንዳገኘ ይነገራ ል።

ልዩ ልዩ የአፍሪካ ሀገሮች አሜሪካ በእርዳታ ስም የሚልክላቸውን ጎጂ ጂ. .ኤ ም.ኦ ሰብል አንፈል ግም እያሉ መልሰው ልከውላቸዋል። በቅርቡ ብዙ ሺህ ቶ ን የአሜሪካን እርዳታ አናስገባም ካሉት ውስጥ ዚምባብዌና ዛምቢያ ይታወሳሉ። ያንን ለማድረግ ነጻነትና ልእልና (ሶ በ ሬ ኒ ቲ) ያስፈልጋል።

ያ ደግሞ እኛ ቤት እጥረት አለብን ። እውነቱን ለመናገር አቹጠን ሸጠናል። ስለዚህም የፈለጉትን በፈለጉ ጊዜ ይጥሉብናል። .

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

21. በኮርፖሬት ካፒታሊስት ግሎባላይዜሽን የግዛት ዘመን፣ መንግስት ሲቢክ ድርጅቶች ዲሞክራሲና ፓርቲ

የኢትዮፕያ አለኝታ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለወቅቱ ግሎባላይዜሽን ሂደት ሳያሰልሱ ቢከታተሉ ጠቃሚ መሆ ኑ አስታዋሽ አያሻውም። ግሎባላይዜሽን ማለት በአጭሩ በኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ የመሬት ርዝመትና ስፋት ተወግዶ ኣለም ትንሽ መንደር እንድትሆን ማድረጉን አስታኮ በመጠቀም የተኀኀመውየኣለም ታላላቁ ህብረ ብሄር ካፒታሊስት ኮርፖሬሽኖች (ኩባንያዎች) -በተለይ አሜሪካውያን በነጻ ገብያ ስም የፈጠሩት በሶብየት ኮሙኒዝም መፈራረስ የልብ ልብ ያገኘ እስከ ዛሬ በአፍሪካ ካየንው ሁሉ የከፋ ልጉም የለሽ የቅኝ ግ ዛት ናዳ ኢምፔሪያሊዝም ነው።

የ ግ ሎ ባ ላ ይ ዜ ሽ ን ለፋፊዎች እንደሚያስተምሩት በዛሬው በኤሌክትሮኒክስ ዘመን የቀድሞ ውበ19 መቶ ክፍለ ዘመን ካፒታሊዝም በፈጠራቸው ሁለቱ የኢኮኖሚ ክፍሎች ማለት ቡርዘውና የኢንዱስትሪ ወዝ አደሩ መሃል በተፈጠረው ቅራኔና ትግል ፤ በፓርቲ ምስረታ መሳሪያነት፣በሲቢክ ማህበራት ምስረታና ትግል፣ ወንድ ሴት ሳይለይ፤ ሃብታም ድሃ ፣ የተማረ ያልተማረ ፣ ሳይለይ፣ለዜጋ ሁሉ የምርጫ መብት ተሰጥቶ፣ ዲ ሞ ክ ራ ሲ በትግል ተመስርቶ፣ ወኪሎቻቸውን መርጠው ፓርላማ ልከው ፣ በፓርላማው አማካኝነት የአሸናፊው ፓርቲ መንግስት ተኀቁሞ፣ በ መንግስቱ ውስጥ በህገ መንግስት የታወ ቀ፣ የአስተዳደሩ፣ የህግ አውጭው ፣ የዳኝነት ፣ ሶስት ረሳቸውን የቻሉ ክፍሎች ነጻነትና መብት ተለይቶ እስካሁን በታላላቁ ምእራባውያን ህብረተሰብብ ዘንድ ሲሰራበት የቆየው ስርኣት ዘመን አልፎበታል ይሉናል። የዌልፌር ስርኣት ፣ በህብረ ተሰቡ ውሰጥ ያለው ችግረኛ ለምግብ ለትምህርት ለጤና ለስራ አጥ ለጡረታ ወ ዘ ተ የሚረዳበት ስርኣት፣የሰራተኞችማህበር የድርድር መብት ጊዜው አልፎበታል ይሉናል። የመኖር አለመኖር ጉዳይ በገንዘብ በንግድ ኩባንያዎ ችሊወሰን ነው ማለት ነው። እነሱ እንደሚሉት አሁን ባለንበት የኤሌክትሮኒክ ዘመን የህዝብ ምርጫ ማንም መሃል ሳይገባ፣ ጊዜ ያለፈበት ፓርቲ ሳያስፈልግ፣ ፓርቲዎች ተወግደው፣ ህዝብ በቀጥታ በኤሌክትሮኒክስ በኢንተርኔት መወያየት ብሎም መምረጥ ይችላል የሚሉ ናቸው። ይህንንም ፕ ሌ ብ ሺ ተሪ ዲ ሞ ክ ራ ሲ ይሉታል ። ህዝቡ ያለ መሃል አጫፋሪ በቀጥታ የሚፈልገውን መሪ የሚመርጥበት እሰካሁን ዲ ክ ታ ተ ሮ ች የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው። በሶስተኛው ኣለም በአፍሪካ ኮምፕዩተር ኢንተርኔት ለማስገባት የሚካሄደው ሩጫ የግሎባላይዜሽን ኀንኀና ባህል ከማስፋፋት ሌላ አንዱ ሌላው ምክንያት ኤሌክትሮኒክ ፕሌብሺተሪ ዲሞክራሲ ሊያዘልሉን ባላቸው ኣላማ ሊሆን ይችላል። እሰከነአካቴው እነዚሁ የግሎባላይዜሽን ሰባኪዎች የማእከላዊ ብሄራዊ መንግስት ዘመን አልፎበታል ይሉናል። ማእከላዊ ብሄራዊ መንግስት ካሁን በጪላ አያስፈልግም ይሉናል። የህ ከሆነ ከላይ ያሰመርንባ ቸው ሁሉ በ ስንት የህዝብ ትግል በብዙ ሰው ህይወት መስዋእትነትና ተጋድሎ የተገኙ የዲሞክራሲ ድሎች ሊፋቁ ነው ማለት ነው.። ይህም ከግሎባላይዜሽን ጋር የተጀመረውን ግብ ግብና መጭውን የትግል ዘመን ይጠቁማል

የታለላቅ ኣለም አቀፍ በተለይ አሜሪካን ህብረ ብሄር ካፒታሊስት ኩባንያዎች የፈጠሩት ግሎባላይዜሽን አፈ ቀላጤ ተደርኀ የሚወሰደው ጃ ፓ ኑ ኬኒቺ ኦህማክ « ½,EY± O–×h‡‰ óêS: ½XÐ•M ¥®˜Qµ• „OYå’‰ > በተባለው መጽሀፋ ወቅቱ መንግስት የሌላቸው ማእከላዊ ተቆጣጣሪ የሌላቸው ሪጅናል (የአካባቢ ሀገሮች) የሚያኀቁቹቸው ነጻ ገብያ እኮኖሚዎች ናቸው ይለናል። በ ተ ጨ ባ ጭ ሲታይ እነዚህ ሪ ጅ ና ል እ ኮ ኖ ሚ የሚባሉት ታላላቅ ኣለም አቀፍ በተለይ አሜሪካን ህብረ ብሄር ካፒታሊስት ኩባንያዎች በተለይ የድሆቹን ሀገሮች እንደልባቸው ያለአንዳች ተቆጣጣሪ የሚገቡና የሚወጡበት እንደ አሰኛቸው የሚዘርፉበት ስርኣት ማለት ነው። ኢትዮፕያውያን የአካባቢ እኮኖሚን ምንነትና ኣላማ በቀላሉ ለመረዳት የአሜሪካኖች «የአ ፍ ሪ ካ ቀ ን ድ» መነግስት ወይም አካባቢ እኮኖሚ ብለው ኢትዮፕያን እርትራን ሱማሌን ጂቡቲን ወዘተ አድርገው መንግስት የሌለበት ኢትዮፕያ እሚባል ብሄር የሌለበት ነጻ የተባበረ ቅኝ ግዛት ለማኀኀም በተከታታይ የሚወሰዱትን እርምጃ ማጤን ነው። ለኣመታት ሲካሄድ የቆየው ኢትዮፕያን በዘር የመከፋፈልና ብሄራዊ መን

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ግስቱ ብሄራዊ ጎንጎ ብሄራዊ ፊደል ብሄራዊ ሃይማኖት ብሄራዊ ባህል ብሄራዊጦር በአጠቃላይ ብሄራዊ የተባለ ሁሉ የሚፋቅበት የማጥፋት ዘመቻ ከዚህ የኢምፔሪያሊስት ኣለማ ጋር ተያይዞ ሊታይ ይገባል። በሱማሌም የአሜሪካ ቅጥረኛ በሆነው በወያኔ ሳቢያ ብሄራዊ መንግስት እንዳይጎጎም የሚደረገው ዘመቻ ሁለ ይህንኑ የአፍሪካ ቀንድ የስብስብ ቀኝ ግዛት ለመመስረት ነው። በአፍሪካ በአጠቀለይ በአሁን ጊዜ በነዚሁ በገንዘብ የናዘዙ የደነዘዙ ኣለም አቀፍ ኩባንያዎች የተጎጎሙ ቅጥረኛ ጦር ሃይሎች በልዩ ልዩ ምክንያት የውስጥ ጦርነት እየከፈቱ መንግስታትን እያፈረሱ የአፍሪካን ሀብት እንቁ፤ ወርቅ፣ቤንዚን በነጻ እየዘረፋ ነው። በአሜሪካ እነዚህን ኮርፖሬሽኖች (ኩባ ን ያ ዎ ች) የሜያስተባብረው፤ ኢትዮፕያን አዘውትሮ የሚጎበኘው <u>፣አሜሪካን ኮርፖሬት ካውንስል</u> የተባለው ድርጅት ነው።

ይህ ነው በግርጅፋ ያለንበት የግሎባላይዜሽን ዘመን አለኝታ ፓርቲዎቻችንን የሚገጥማቸው።

<u>22. ኢትዮፕያዊነት - የወቅቱ ጥማት ፣ከጥንታዊት ኢትዮፕያ መጎንጨት ፤ የትምህርትና የባህል ፖለሲ ጉዳይ</u>

ከጥቂት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮፕያዊያውያን፤ በተለይ በውጭ ሀገር ፣ በያለበት ፣ ጾታ እድሜ ሳይለይ፣አስመሳይ አጉል የምእራባውያን ተምህርት የምእራባውያን «ስልጣ ኔ» አቀባባይ መሆን ያንገሸገሻቸው የጎዳቸውመሆኑን ተረድተው፣ታሪካችን ተጠንቶ ባህላችን ተጠንቶ እኛም ልጆቻችንም ወደ ኢትዮፕያዊነት መመለስ
አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። ይህ የስደት ኑሮ ነጸብራቅ ሳይሆን በተጨባጭ የምእራባውያንን የሚስዮናውያንን ዘረኛ በቅኝ ግዛት ፖለቲካ ላይ የተመሰረተ፣ የኢትዮፕያን ስም በማንጃሰስ አዋርደው፣ኢትዮፕያን በዘር ከፋፍለው ሊገዝዋት የሚጥሩ መሆናቸውን፤ በተለይ የወቅቱ ግሎባላይዜሽን (ወይም አ ሜ ሪ ካ ና ይ ዜ ሽ ን) የኣለምን ህዝብ ሁሉ ጨፍልቆ በአንድ መልክ በአንድ ጎንጎ በአንድ ሃይማኖት፣ እንደ ሮቦት (አርቲፊሻል ሰው) ባንድ ቅርጽ ለገብያ እንዲመቻች አድርጎ ሊሰራን ጥድፊያ ላይ መሆኑን ካጤኑና ፤ በተለይ ላለፋት አሰራ ሁለት ኣመታት ሀገር ቤት በወያኔ የሚፈጸመውን የባህል ቅርሶቻችንን ናዳ ከተመለከቱ በጪላ የደረሱበት፣ ከረዝም ጊዜ ግንዛቤ የመነጨ ስሜት ነው ብለን ስለምናምን የህን ኢትዮፕያዊያውያንን በእጅጉ የሚያሳስባቸው የባህል ጉዳይ በአራት ከፍለን እንመለከተዋለን

1. የኢትዮፕያ ጥንታዊ ብሄራዊ የግእዝ ባህልና ትምህርት

2. ብሄራዊ ዘመናዊ ምእራባዊ ትምህርት (ስልጣኔ) ና ኢትዮፕያዊነት ከምኒልክ እስከ ቀዳማዊ ታይለ ስላሴ

3 የሁለቱም በጠላቶቻችን የረጅም ጊዜ ፕላን ውስጥ ገብተው ቀስ በቀሰ አንዳንዴም በአዋጅ በአሰደንጋጭ ፍጥነት መናድ መፍረስ መቦርቦር መዘረፍ

4. ልንገነባው የምንፈልገው በግእዝ ባህል ላይ የተመሰረተ፣በጥንቱ የገበሬያችን ከፍተኛ የስልጣኔ ደረጃና ምርት ላይ የተመሰረተ፣ አኩሪ የኢትዮፕያዊነት እድገት ነጸብራቅ የሆነ፣ አፍሪካዊ ባህልና ትምህርት ይዘት

ይህ ሰፋ ያለ ጉዳይ በመሆኑ እዚህ ላይ ስለጥንታዊ የግእዝ ባህላችን አንዳንድ ማሰታወሻዎች አቅርቤለጊዜው እዚህ ላይ አቆማለሁ።

<u>ጥንታዊ የ-ግእዝ ባህላችን ፣</u> ግእዝ 4000 ኣመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ቅርጹ ሰዋሰውና የቃላት ብዛቱ ከፍተኛ እድገት የደረሰ ከመጀመሪያዎቹ ጥንታዊ የሰው ልጅ ጎንጎዎች አንዱ መሆኑ ይታወቃል። የኢትዮፕያም ጥንታዊ ብሄራዊ ባህል የምንለው ከግእዝ ተያይዞ የመጣውን ነው። በ 4000 ኣመት ከ ክ ር ስ ቶ ስ በ ፊ ት የሪያዎ ምሰ (ይ)728 ምሰ (

ሆነ በጨላ በሺሆች የሚቆጠሩ በሳቢያን በግሪክና በግእዝ ድንጋይ ላይ የተቀረጹ ጽሁፎች ተገኝተዋል።እነዚህም ስለ ኢትዮፕያ ህዝብ ተጨማሪ መረጃ ይሰጡናል።

ሆኖም የምናውቀው የግእዝ ባህላችን ታላቁ ወቅት ከክርስቶስ ልደት እስከ 7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አክሱም ከቀይ ባህር ወደባችን ከአዱሊስ ጋር ባበቡበትና በኣለም ከታያላን መካከል ከሮምና ከፋርስ ጎን በሚቆጠሩበት ዘመን ነበር። በዚህ ወቅት ነበረ የክርስትና ሃይማኖትም ኢትዮፕያ የገባው (350 ኣም አ ካ ባ ቢ) ። የክርስትና ሃይማኖትም ጥንታዊውን ግእዝን መሳሪያው በማድረግ ከጥንታዊ የኢትዮፕያ የአምልኮት ሃ ይማኖቶች ከኦሪት ሃይማኖት (ብሉይ ኪዳን) ጋር ተዋህዶ በየጊዜውም ኢትዮፕያ ውስጥ የሚመሰረቱትን የህዝባችን ሃይማኖቶች (እስልምናና የጋዳ ጋላ አምልኮት ሳይ ቀር) በማዋ ሃድ አስከ ዛሬ ሃይማኖታችን የኢትዮፕያዊነታችነየባህላችን ምሶሶ ሆኖ ቆይቾል። የክርስትና ሃይ ማኖት ባህላችን፤ የእጅ ጽሁፋችን ታሪክ ስነ ጽሁፋችንና፤ ጥንታዊው የመጽሀፍ አዘገጃጀት፣ የብራና ወረቀታችን አዘገጃጀት፤ የብራና ስእሎቻችን፤ የቀለሞ ቻችን አዘ ገጃጀት እንዲሁም ሙዚቃችን በቴክኒካቸውና በውበታቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ባስገኙት እድገት ኣለምን ማስደነቅ ጀምረው ነበር። በሚያስገርም ሁኔታ በጽሁፍ የቀረልን ከጥንታ ዊዎቹ አድናቂዎቻችን በ615 አከባቢ ነቢዩ መሀመድ እስልምናን በአረቢያ መሰበክ እንደ ጀመሩ ገናከመሰረቱ በአካባቢው ከደረሰባቸው ተቃውሞ ና ክትትል ለማምለጥ ከነቤተሰቦቻ ቸውኢትዮፕያ «በ ስ ደ ት» መጥተው ኢትዮፕያ በነበሩበት ጊዜ የሚያስታውሱት አድናቆ ት ነው። አል ታ ባ ሪ እንደጻፈው

> « በነቢዩ መሀመድ ህይወት መጨረሻ ላይ፣ ሚስቶቻቸው ፣ የአማኒዎች እ ናቶች ፣ አልጋቸውንከበው ኢትዮፕያ በነበሩበት ጊዜ ያዩትን የቤተ ክርስትያናቱ ንና በውስጣቸው የተሳሉትን ስእላት
> ውበት - በተለይ የአክሱም ጽዮንን እያነሱ ይጫወቱ ነበር» ብቾል

በቅርቡ የተለየን ወንድማችን ዶክተር ስርግው ሃብለ ስላሴ በኢትዮፕያ ስለጥንታዊ
የብራና መጽሀፍ አዘገጃጀት በጣም የሚደነቅ ትንሽ ጥናት ትቶልን ሄኖል። በኣለም ለመ ጀመሪያ ጊዜ በግብጽ (አሌክሳንድርያ )ና በሲሪያ በፓፒሩስና በብራና መጽሀፍ ማዘጋጀት የተጀመረው በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ነ ው። ግሪኮችም የፓፒ ሩስና የብራና መጽሀፍ አዘገጃጀት የወሰዱት ከግብጽና ከሲሪያ ነው። ኢትዮፕያ ውስጥ የፓፒሩስ ዛፍ በአባይና በዝዋይ አካባቢ ቢገኝም ለጀልባ ስራ እንጂ ወደ ወረቀትነት ለውጠን ወይም ከግበጽ አሰመጥተን ለጽሁፍ ስለመጠቅማችን እሰካሁን የተረጋገጠ መረጃ የለም። በብራ ና መጽሀፍ ዝግጅት ግን ኢትዮፕያ ከግብጽና ከሲሪያ ቀጥላ ከኣለም የመጀመሪያዎቹ አንኖ መሆኑ በኣለም ታላላቅ መጽሀፍት ቤት ኤክስፐርቶች የተ ረጋገጠ ነው። እንደ ስርግው አባባል የብራና መጽሀፍ ሀገራችን የተስፋፋው በ5ኛ ው መቶ ክፍለ ዘመን ፱ኙ ቅዱሳን ከሲሪያ ወደ ኢትዮፕያ ከመጡና መጽሀፍ ቅዱስ ከዳር አስከዳር ወደ ግእዝ መተርጎም በማሰፈለጉ ነው። ዘመኑ ከፋርስ በጨላ የግሪክ (ሄ ሌ ን ሰት) ኣለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ወቅት ስለነበረ ገብጽና ሲሪያም በግሪክ ተይዘ ው ስለነበር ፣ አክሱም ና አዱሊስም በግሪክ ሄሌኒሰት ጥላ ሰረስር ሰለ ነበሩ የግሪክ ጎንጎ በምስራቁ የሰለጠነው ኣለም የተስፋፋበት ጊዜ ነበር። የኢትዮፕያ ንጉስ ዞ ሰ ካ ለ ስ ግሪክ ይነጋገር ነበር ተብቾል። ጨላም ከግሪከ ቀጥሎ የሮም ኢምፔሪያሊዝም ከ ተጎጎመ በጨላ የግሪክ ጎንጎ የበላይነት ቀጥቾል። በዚህ ምክንያት ከግሪክ ወደ ግእዝ ከ ተተረጎሙት መጻህፍት ሌላ ወደ ግእዝ የተገለበጡት የጽህፈት መሳሪያ ቃላት አብዛኛ ው የተወሰዱት ከግሪክ ነው። ብራና ራሱ ከግሪክ «ሜንብራና»የተወሰደ ነው ፥ ቀለም በግሪክ ብእር ማለት ሲሆን እኛ ትርጉሙን ለውጠን ብእሩ የሚጠቀስበትን ፈሳሽ «ቀለም» ብለነዋል። ብእር ራሱ ከሴማዊ ጎንጎ የተወሰደ ነው። አንድ የጥንታዊ መጽሃፍ ት ኤክሰፐርት (ግ ሮ ህ ማ ን) በጥንት ጊዜ ጎረቤቶቻችን አረቦች ስለብራና መጽሀፍ አዘገጃጀት የተማሩት ከኢትዮፕያ አንደሆነ ያረጋግጣል። ምክንያቱም የኢትዮፕያኖች ቴ ክኒክ ቀላል አሰተማማኝና ውበት ያለው ሆኖ ስላገኙት ነው ተብቾል። «መጽሀፍ» የ ሚለው ቃል ጭምር ወደ አረብኛ የተወሰደው ከገእዝ ነው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ብለው ( ጠላቶቻችን ) ተቃውመዋል»

ለመደምደም ያህል ባለኝ የተወሰነ አቅም፣ እውቀትና ልምድ ምን ግዜም ለኢትዮፕያ ነጻነት አንድነትና እድገት ለመተባበር ዝግጁ ነኝ። ከማክበር ሰላምታ ጋር።

ኣለሜ እሸቴ


አድራሻ

ሃቁ. ሀሺሲሻሲ ሄቂስሲቃሲ
ሂ.ሙ 90/ 02 ሀቄቁሲሺሶሸ
00167ማሸሻር , ሉቃርሺቡ


ማ ስ ታ ወ ሻ ይህን ጽሁፍ በተቻላቸሁ መጠን አባዝታችሁ ለኢትዮጵያ ህዝብ አ ዳርሱልኝ፤ አስረዱልኝ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የግእዝ ባህላችን
ኩራት
ሶል
ስ ረ ግ ው
አ ለ ማ የ ሁ ሞ ገ ስ
ግ አ ዝ
ብ ራ ና መጽ ሀፍ
ቤ ተ ክ ር ሰ ት
ዝ ር ፍ ያ
ገረክ ላቲ ን
ፊ ደ ል
ታሪክ
ምእራባውያን
መጽ ሀ ፍ ቅ ዱ ስ
ታ ዜ
ሚሲ ዮ ና ነ ው ያ ነ
ግ ሎ ባ ላ ይ ዜ ሽ ን አሜ ሪ ካ ና ይ ዜ ሽ ን ባ ህ ል ቀንቀ ሃ ይ ማ ኖ
ት ሙ ዚ ቃ ወዘተ

ብሄራዊ ባህል ተደምስሶ ት ል ቁ ሬ ዚ ስ ታ ን ስ ባ ህ ል

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ኢምፔሪያሊዝምና ውድቀታችን

7. በታሪክ የመጀመሪያው የፋርስ (ኢራን) አኬሜኒድ የተባለው ኣለም አቀፍ
ኢምፔሪያሊዝም ከተፈጠረ ከ500 ቅድመ ክርስትያን ዘመን ጀምሮ በቀይ ባህርና በአባይ
ወንዝ አማካኝቶ ግብጽን የወረረ የኣለም ታያላን ሁሉ የኢትዮጵያን ነጻነትና እድገት ሲፈ
ታተን ቆይቾል። እ ሰ ከ ዛ ሬ ድ ረ ስ ስ ለ ታ ላ ቁ የእክ ሱ ም ስለጣ ኔ ፍ
ጻ ሜ ምንም የምናውቀው ነገር የለም። ያለን ፍነጭ ቢኖር ገናያልተገባደደ ጥናት ቢሆ
ንም አዱሊስ ከግሪክ ዘመን ጀምሮ ሲያገለግል የቆየው ታላቁ የኣለም ንግድ ኤምፖሪየ
ምና የኢትዮፕያ የቀይ ባህር በር በጦር ተወግቶ እንደሌለ የፈራረሰውና ፣ የአክሱምም
ከተማ ራሱ መጎጎም በማይችለው ታላቅ ጦ ር ተወግቶ የተፈረካካሰው በ576 አካ
ባ ቢ ኮስሮ የፋርስ ሳሳኒድ ንጉስ ሰራዊት ከካሌብ ዘመን ጀ ም ሮ አረቢያን ይገዛ
የነበረውን የኢትዮጵያ ጦር ወግቶ አሸንፎ እባርሮ የ ቀ ይ ባ ህ ር ን ተሻ ግ ሮ
የኢትዮጵያን ወደብ ለረዝም ጊዜ በጎሚነት ይገዛ ነበር ከሚለው መረጃ ጋር ይያያዛል።
በዚሁ ዘመን በተከታታይ ትግረ የተባለው በኤርትራ ሰሜናዊ ጠረፍ ቆላ የሚኖር ዘላ
ን ከብ ት አርቢ ህዝብ አክሱምን በጎሚነት መውረርና መሰፈር፤ ከዚህ በጨላ የአክ
ሱም ስልጣኔ ፍጻሜ ፣ የግእዝ ህዝብና ግእዝ ጎንጎ ሲክስም፤ ትግራይና ትግርኛ ስፍ
ራውን መውሰዳቸው ከዚሁ ከፋርስ ወረራ ጋር አብሮ የሚታይ ነው።

ገና በጥናት ላይ ብንሆንም የሮማውያን የኣለም ታያል መንግስትን በቀይ ባህርና በምስራ
ቁ (ህንድና ቻይና) ታላቅ ንግድ ሳቢያ ለረጅም ጊዜ ይፎካከረው የነበር ሳሳኒድ የተባለው
የፋርስ ሁለተኛው ታላቅ ኢምፔሪያሊዝም (224-651) ከሜሶፖታሚያ (ኢራክ) ጀምሮ
እስከ ህንድ ድረስ የነቢዩ መሀመድ አረብ እስላማውያን ተከታዮች ኣለም አቀፍ ታያል
ኢምፔሪያሊስት መንግስት እስከ መሰረቱበት ድረስ ይገዛ ነበር። ግብጽን የቅኝ ግዛት አ
ድርጎ የነበረው ሮም የቀይ ባህርና አረብያን መቆጣጠር በመፈለጉ በወቅቱ ሀያል ከነበረ
ችው ኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት ይመስርታል። ይህም እስከ ዛሬ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪ
ክና ጂኦ ፖለቲካ ለመመስረት ምክንያት ይሆናል። በወቅቱ ሮም ኢየሩሳሌምን ከመግዛ
ቾ በላይ እስከ ሜድትራኒያን ባህር ጠረፍ (ሲሪያን ሌባነንን ቱርን ወይ ም ታይርን) ጨም
ሮ ግዛቾ ስለነበሩ የክርስትያን ሁሉ የበላይ ተቆርጎሪ ነኝ የሚል ፖለቲካ ነበራት። በሮ
ምና በኢትዮጵያ መሃል የተፈጠረው ወዳጅነት ማሰሪያ እንዲሆን ሲባል ነው በ 4ኛው
መቶ ክፍለ ዘመ ን ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከታይር የገባው ብለው የሚያምኑ ጥቂት አ
ይደሉም። ያም ሆነ ይህ የክርስትና ኢምፔሪያሊስት ፖለ ቲካ ለጊዜው መጥፊያችን ይሆና
ል። ሮምና ኢትዮጵያ በመተባበር በሳባና ሂሚያር (የዛሬው የመን) ያሉት ክርስትያናት በአ
ይሁዳውያን ሳቢያ ጥቃት ደረሰባቸው ተብሎ የጦር መረከቦች ይሰሩና በተጨማሪ ከህንድ
ይገዙናየካሌብ ጦር ቀይ ባህርን ተሻግሮ አረቢያ ይ ዘ ም ታል። አረቢያንም ለተወሰኑ
ኣመታት ይገዛል። ዮ ፐየኢትዮጵያወ ግዛት በአረቢያ በጸናበት ዘመን ከል ዩ እንጨ
ት የተሰሩት በወረቅ ያጌጡ በስእላት ያሸበረቁ ቤተ ክርሰትያና ትና ህንጻዎች ለበዙ ዘ
መን በአድናቆት እንደ ላንቲካ ይታዩ ነ። በመጨረሻ የሳስኒድ ፋርስ ንጉስ በወቅቱ የኢት
ዮጵያን ንጉስ መዳከም ጠብቆ ሳባና ሂሚያርን ከኢትዮጵያ ነጻ አወጣለሁ በማለት አረቢያ
የነበረውን የኢትዮጵያ ጦር ድምጥማጡን ያጠፋዋል። ከዚህ በጨላ ያለው ገና ጥናት የ
ሚጠብቅ ነው። የምናውቀው በዚሁ ዘመን አካባቢ አዱሊስ ከግሪክ ዘመን ጀምሮ
ሲያገለግል የቆየው ታላቁ የኣለም ንግድ ኤምፖሪየምና የኢትዮፕያ የቀይ ባህር በር በጦ
ር ተወግቶ እንደሌለ ይ ሆ ና ል። የአክሱም ከተማ ረሱ መጎጎ ም ከማይችለው ታላቅ
ጦ ር ተወግቶ ከተማ ው ከስር ተፈንቅሎ ህንጻዎቹ ፈራርሰዋል። በዚሁ ዘመን በተከ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ታታይ ትግረ የተባለው በ ኤ ር ት ራ ሰ ሜናዊ ጠረፍ የሚ ኖር ቆላ ከብ ት አርቢ ህዝ ብ አክሱምን በጎሚነት ወሮና ሰፍሮ የግእዝ ህዝብና ግእዝ ጎንጎ ሲከስም ትግራይ ና ትግርኛ ይተካሉ። በጥንት ጊዜ ትግረ ወይም ትግራይ የሚ ባ ለወው አክሱምን አድዋ ን ይዞ በሰተ ደ ቡብ እስከ ወርኢ ወንዝ ያለው መሬት ነበር። ይህ የአክሱም ስልጣኔ ፍጻሜ ይሆናል። ይከው ዘላን ትግረ እስከ ሀረርና ደቡብ መሃል ሀገር ፈልሶ በመስፈ ር ከሃገሬው ተደባልቆ ፤ አደሬ ፣ ትግረ ወርጅ እንዲሁም ለጉራጌ ጭምር ከትግረ የ ተቀራረቡ ሴማዊ ተናጋሪዎች መፈጠር ምክንያት ሆንዋል ተብሎ ይታመናል። ይህ በዚህ እንዳለ ሆኖ ማን ነው ሃይለኛው የውጭ ጦር ወራሪ ብለን ስንጠይቅ በድጋሜ የምናተኩረ ው ወደ ፋርሰ ሳሳኒድ ጦር ነው፣ 676 የነጉስ ስም - .አረብ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com